SEATTLE PARKS AND RECREATION

አዲስ ዜና

Mike McGinn, Mayor
Christopher Williams, Acting Superintendent

ወዲያዉኑ መሰራጨት አለበት **ኦክቶበር** 28, 2013

የሚገናኙት፤ Karen O'Connor (206) 684-7241
email karen.o'connor@seattle.gov

የ Seattle Parks Legacy Plan Citizens Committee ሕዝባዊ ችሎት ሊያካሂድ ነው

የ Seattle Parks and Recreation **ለወደፊት ያለውን የገንዘብ አሰባሰብ ምርጫዎችን እንዲያውጠነጥን የተመረጠው የ** Parks Legacy Citizens Advisory Committee**፣ ሐሙስ፣ ኖቬምበር** 7 2013**፣ በ** 6 **ከሰዓት በኋላ ላይ፣ በ** Miller Community Center **ላይ ወደ ሚደረግ የማሕበረሰቡ የህዝብ የችሎት ስብሰባ ላይ እንዲሳተፉ ጋብዞዎታል።**

የ Seattle Parks and Recreation**፣ በችሎቱ ላይ እንዲሳተፉና እንዲናገሩ፣ የውጭ ዜጋ ነዋሪዎችን (ኢሚግራንቶች)፣ ስደተኞችን፣ የተለያዩ የቀለም ቆዳ ያላቸውን ሰዎችንና፣ ሌሎች የተለያዩ ማሕበረሰቦችን በልዩ ክብር ይጋብዛል። ከነዚህ መሕበረሰቦች የሚሰባሰብ አስተያየት፣ ለ** Seattle **የህዝብ ፓርኮችና የመዝናኛ ፕሮግራሞች ሁሉንም አቀፍ የሆነ መጪን ለመቅረዝ በእጅግ አስፈላጊ ነው።**

በቀረበው የዲፓርትመንቱ የ Race and Social Justice Initiative (RSJI) **መርህ መሰረት፣ እንደ የፓርኩ የቅስቀሳ ጥሪ አንዱ ክፍል፣ የ** Change Team **ቡድኑ፣ በታሪክ ባለፉት ግዜያት ዝቅተኛ-ውክልናን ያገኙ ወደ ነበሩ ማሕበረሰቦች በመሄድ፣ ሃሳባቸውን ለመቀበል ቅርርብ ለማድረግ ሙከራን ፈጽሟል።**

የ Change Team **ቡድኑ ዓላማ፣ ባለፉት የእቅድ ማውጣት ሂደቶች ላይ ለመሳተፍ ዕድል ላላገኙ ማሕበረሰቦች፣ ሃሳባቸውን የማቅረብ ዕድልን መስጠት ነው። ማሕበረሰቦች ወደ ሚሰበሰቡበት፣ መገናኙበትና የሚኖሩበት ቦታዎች በመሄድ፣ የ** Change Team **ቡድኑ፣ ወደ ሂደቱ ሙሉ አዳዲስ ድምጾችን ማምጣት ችሏል።**

በአሁን ወቅት፣ ለወደፊት በሚካሄዱ ለፓርክ ገንዘብ መሰብሰብያ የድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ እንዲገቡ፣ በሀሳብ ደረጃ የቀረቡ 37 **የመዋዕለ ነዋይ ሀሳቦች (የገንዘብ መሰብሰብያ ሀሳቦች) ሀሳቦች ቀርበዋል። የነዚህ** 37 **የቀረቡ የመዋዕለ ነዋይ ሀሳቦች፣ ቅደም ተከተላዊ አፈጻጸም የሚካሄደው በሶስት ንኡስ ኮሚቴዎች ይሆናል፤ በመካሄድ ላይ ያሉ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች፣ አዲስ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶችና ሽሪክነቶች። በኖቨምበርና ዲሴምበር**

ላይ፣ የንኡስ ኮሚቴው ቅደም ተከተላዊ የስም ዝርዝሮች፣ በ Legacy Committee ው ወደ አንድ የቅደም ተከተላዊ ዝርዝር ሰንድ እንዲጠቃለል ይደረጋል።
በመካሄድ ላይ ያሉ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ኮሚቴው ቀዳማዊነት የተሰጣቸው የመዋዕለ ነዋይ ተግባሮች በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉት፣ የፓርክ ሜይንተናንስና የአዛዎንትና ወጣቶች የማሕበራዊ ማእከል ፕሮግራሞች ናቸው። በአዲስ ፕሮግራሞች ንኡስ ኮሚቴው ቀዳማዊነት የተሰጣቸው የመዋዕለ ነዋይ ተግባሮች በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉት፣ አዲስ ፓርኮችንና ፕሮግራሞችን መፍጠር፣ እንዲሁም የፓርክን ደህንነት ማሻሻል ናቸው።
የሽሪክነት (ፓርትነርሺፕ) ኮሚቴው፣ እንደ የዱር እንስሶች መናህርያ (ዙ) እና አኳሪየም የመሳሰሉ ያለ ትርፍ የሚሰሩ ድርጅቶችን ከከተማው ኤጀንሲዎች ጋር በሽሪክነት ለሚያደርጓቸው ስራዎች ገንዘብ በመሰብሰብ ላይ ሰርቷል።

ከዚህ በተጨማሪም፣ ኮሚቴው፣ እንደ የአጭር-ግዜ፣ የረጅም ግዜንና ዘላቂ ግብሮችን ስለመሳሰሉ አማራጭ የገንዘብ መሰብሰብያ መንገዶችንና ስለ ሜትሮፖሊታን የፓርክ ዲስትሪክት አስመልክቶ የቀረቡ አስተምህሮዎችን ሰምቷል። ኮሚቴውን እነዚህን አማራጮችን በዝርዝር ይወያይባቸዋል። ይህ ከመሆኑ በፊት ግን፣ ኮሚቴው ከ Seattle ነዋሪዎች አስተያየቶችን ለመስማት ይፈልጋል።

በኖቨምበር 7 ላይ በሚካሄደው ችሎት፣ ሁሉም ማህበረሰቦች ለወደፊት በሚኖሩ የ Seattle ፓርኮች ላይ እንዲሳተፉ ዕድል ይሰጣል። የ Parks Legacy Citizens Advisory Committee በ 2014 በሚኖረው የድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ መስፈር ያለባቸውን የገንዘብ መሰብሰብያ መርጫዎችን ከማስፈራቸው በፊት፣ ከኢሚግራንቶች፣ ስደተኞች፣ የተለያዩ የቆዳ ቀለም ካላቸው ሰዎችና ከተለያዩ ማሕበረሰቦች አስተያየት መቀበል ይኖርባቸዋል። የ Legacy Committee ው ስራን አስመልክቶ መረጃ በዚህ ዌብሳይት ላይ ይገኛል፤
http://www.seattle.gov/parks/legacy/committee.htm

የ Seattle Parks and Recreation፣ 6,200 —ካሬ ሜትር ያለውን፣ 465 ፓርኮችንና ሰፋ ያሉ የተፈጥሮ መልከዓ ምድሮችን ያካተተ የፓርክ ሲስተምን ያስተዳድራል። ፓርኮች የስፖርት ሜዳዎችን የቴኒስ ሜዳዎችን፣ የመጫወቻ ቦታዎችን፣ ልዩ የአበባ ጓሮውችንና ከ 25 ማይሎች በላይ የሚሆኑ ጎዳናዎችንና 120 ማይሎች የመተላለፍያ መንገዶችን (ትሬይልስ) ያቀርባል። ፓርኮች በተጨማሪ፣ 26 የማሕበራዊ ማእከሎችን፣ ስምንት የቤት ውስጥ የመዋኛ ገንዳዎችን፣ አራት የመልከዓ ምድራዊ የትምህርት ማእከሎች፣ ሁለት አንስተኛ የስነ ጥበብ ማእከሎች፣ አራት የጎልፍ ሜዳዎች፣ ከፍት ሜዳ ላይ ያለ ስታዲዩምና ሌሎችን በተጨማሪ፣ ያስተዳድራል። የ Citizens Advisory Committee ፣ ለነዚህ አያሌ አገልግሎቶችና ተቋሞች መሰብሰብ ስላለበት የገንዘብ አሰባሰብ ቅደም ተከተል የእርስዎን አስተያየት እየጠየቀ ነው።

ከንቲባውና ምክር ቤቱ፣ የ Parks Legacy Plan (http://www.seattle.gov/parks/legacy) ንድፈ ሓሳብን የሚገመግምና፣ ለፓርኮችና የመዝናኛ ተቋሞችና ፕሮግራሞች ማንቀሳቀሻ፣ ለጥገና፣ ለእድገትና ለመግዣ የሚሆኑ፣ ሊኖሩ ስለሚችሉ አማራጭ የገንዘብ አሰባሰብ መንገዶችን አስመልክቶ አስተያየቱን የሚሰጥ ኮሚቴ መሰረቱ። የተከለሰ የ *Parks Legacy Plan: Draft Goals and Strategies* ግልባጭ፣ ከፕሮጀክቱ ዌብሳይ ዳውንሎድ ማድረግ ይቻላል። ኮሚቴው፣ ለከንቲባውና ለምክርቤቱ ማቅረብ ያለበትን የመጀመርያ ሀሳቡን በዲሰምበር 2013 ላይ አዘጋጅቶ ያቀባል።

የኮሚቴ አባሎቹ የሚከተሉት ናቸው፤ Barbara Wright፣ ኣጋር ሊቀመንበር፤ Charlie Zaragoza፣ ኣጋር ሊቀመንበር፤ Thatcher Bailey፣ Steve Daschle፣ Juli Farris፣ Bill Farmer፣ Thomas Goldstein፣ Jessie Israel፣ Diana Kincaid፣ Michael Maddux፣ Brice

Maryman፣ Yalonda Gill Masundire፣ Mustapha Math፣ David Namura፣ **እና** Erika Nuerenberg-Melroy።

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህንን ዌብሳይ ይመልከቱ
http://www.seattle.gov/parks/legacy/committee.htm።

በስብሰባው ላይ ልዩ መገልገያዎች ወይም የማስተርጎም አገልግሎቶች የሚያስፈልግዎ ከሆኑ፣ ከ Susanne Rockwell **በ** susanne.rockwell@seattle.gov **ወይም** 206-733-9702 **ይገናኙ።**

# # #